# እንድምታ

በየሶስት ወሩ በኢትዮጵያውያን መጻሕፍት ክበብ የሚዘጋጅ የስነጽሑፍ ልሳን — ቁጥር 2


## ከአዘጋጆቹ

ለሁለተኛው እትማችንና ለዚሁ አገር አዲስ አመት እንኳን አደረሳችሁ:: ይህችም ቁጥር መውጣቷ ልሳናችን አንዴ ብቅ ብለው ከተሰወሩት መጣጥፎች እንዳትፈረጅ አድርጓታል:: እናም አንድምታችንን ረጅም እድሜ ይስጥልን እንላለን::

የምሥራች እያልንም ክበባችን ባጭር ጊዜ በአባላቱ ድጋፍ እስከ መጽሐፍ ማሳተም ድረስ ያበቁትን ክንውኖች በአዲሱ <u>ዜና አንድምታ</u> አምዳችን አስፍረናል:: እንዲሁም የቀደምት ምሁራን ያቀረቡትን የስነጽሑፍ ሂስ የሚያወሳ አምድ ጨምረናል::

ከደረሱን አስተያየቶች እንደተረዳነው ልሳኑንና መጽሐፎቹን አገላብጣችኋል፤ አንዳንዶቻችሁ ደግሞ ጭራሽ የሶስት ወሩን በሳምንት ፈጥማችሁታል:: ስለዚህም ነው ለሚቀጥሉት ወራት የተመረጡት መጻሕፍት ደጎስ ደጎስ ያሉት::

በዚህ እትም እንግዳችን ያደረግነው ሩቅ አሳቢውን ደራሲ እንዳለጌታ ከበደ ነው:: የእንዳለጌታን አጭር ልብወለድ ስብስብ (<u>ከጥቁር ሰማይ ስር</u>) ለታኅሣስ መርጠንላችኋል:: አስራ ሁለት ሴት ገጣሚያን የያዘውን <u>እኛ 170 ግጥሞች</u> የተሰኘ መድበል ለጥር ታጭቷል:: ለወርሀ የካቲትም የአንጋፋው ደራሲ የአዳም ረታን መጀመሪያ ረጅም ልብወለድ ስራ <u>ግራጫ ቃጭሎች</u>ን ይዘናል::

መልካም ንባብ::

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| ቆይታ ከእንዳለጌታ ከበደ | 1 |
| ከጥቁር ሰማይ ስር | 2 |
| ሴት ገጣሚያን በአንድነት | 3 |
| ግራጫ ቃጭሎች | 4 |
| የት ይሆን ያነበብኩት? | 6 |
| ስለድርሰት ምን ተብሏል? | 7 |
| ዜና አንድምታ | 8 |




ባለፉት አመታት ከደመቁት የስነጽሑፍ ኮከባት መሀል ወልቂጤ ያፈራችው እንዳለጌታ ከበደ አንዱ ነው:: በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ፣ በ<u>እፍታ</u>ና በ<u>ክንፋም ህልሞች</u> ካቀረበው ስራዎቹ ሌላ በ1996 ዓ.ም. <u>ከጥቁር ሰማይ ስር</u>ን እንዲሁም በያዝነው አመት <u>ዛጎል</u> የተሰኘ ረጅም ልብወለድን አቅርቦልናል:: እንዳለጌታን በቅርቡ ከአዲስ አበባ በስልክ አግኝተነው ነበር::

***እንዴት ወደ ስነጽሑፍ አለም ገባህ? ከየትስ ጀመርክ?***

ለመጀመሪያ ጊዜ ግጥም የጻፍኩት ሰባተኛ ክፍል እያለሁ ነው:: አንድ ጓደኛችን ግጥም መድረክ ላይ አቀረበ:: እና ያኔ ተጨበጨበለት፤ በጣም ሙገሳ በዛለት:: እኔ ደግሞ ያቺ ግጥም ከጋዜጣ እንደተወሰደች አውቃለሁና እንዴት ባልሰራው ስራ የኔ ነው እያለ ጉራውን ይቸረችርብናል ብዬ ተናደድኩ:: ጓደኞቼ ደግሞ ታዲያ በዚህ እድሜው ከየት ሊያመጣ ይችላል፣ ከባድ እኮ ነው ብለው መልሰው እኔን ተቆጡኝ:: እኔም ይህን ያህል ከባድ አይደለም ብዬ አንድ ግጥም ጽፌ ለመምህሩ ሰጠሁ:: መምህሩ ግን ከድርሰቱ ይልቅ የወደደው እጅ ጽሑፌን ነበር:: ቢሆንም አበረታቶኝ ለወላጆች ቀን ዝግጅት አቀረብኩት::

እንዲሁም ቤት የምሰማውን ተረትና ታሪክ ቀይሬ አሻሽዬ ለሰው አወራ ነበር:: አሁን ሳስበው ወደ ድርሰት ማዘንበሉ ያኔ የተጀመረ ይመስለኛል:: ቤተ ክርስቲያንም አካባቢ እሄድ ስለነበር የቅዱሳን ገድልና ታሪካዊ ነገሮች አነብ ነበር - በተለይ ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ የሚያሳትሟቸውን:: የጸሎት መጽሐፎቹ ግን የዛን የአራተኛ ክፍል ያለሁበትን ምኞቴን አልያዙም ነበር:: ያኔ ምኞቴ በትምህርቴ በጣም ጎብዤ አባቴን ማስደሰት ነበር:: የጸሎት መጽሐፎቹ ግን የሚሉት ጳጳሱን ባርክ እንዲያ የመሳሰለውን ነው:: በልጅነት አእምሮዬ የጳጳሱ መባረክ ጥቅሙ ስላልገባኝ ትናንሽ የጸሎት መጽሐፎች እጽፍ ጀመር - እኔ መሆን የምፈልገውን ቤተሰቦች ከኔ የሚጠብቁትን:: «እግዚአብሔርዬ ከተማሪዎች ሁሉ የተሻለ ውጤት እንዲኖረኝ አባቴም በኔ ደስ እንዲለው አድርግልኝ» እያልኩ እጽፍ ነበር:: ከዛም ቀስ በቀስ ወደ ልብወለድ ንባብ ገባሁ::

***የትኞቹን የልብወለድ ጽሑፎች ታነብ ነበር?***

መጀመሪያ ያነበብኩት <u>ሽልንጌን</u> የሚል አማርኛ መጽሐፋችን ውስጥ የሚገኝ አጭር ልብወለድ ነበር:: ከዛም ሳንቲም ሳገኝ - ያኔ መጽሐፎች 3.50 ወይም 4.50 ያወጡ ነበርና - ያገኘሁትን ሳላማርጥ አነብ ነበር:: መጀመሪያ በጣም የወደድኩት አጭር ልብወለድ የስብሐት ገ/እግዚአብሔርን <u>አምስት ስድስት ሰባት</u> ነበር:: እሱ ግን ታዋቂ መሆኑን ያወቅኩት አስረኛ ክፍል እያለሁ የአማርኛ መምህራችን ከታዋቂ ደራሲዎች አንዱ ስብሐት ነው ብሎ ሲነግረን ነው:: ያኔ መምህሩ እኔ የምወደውን ደራሲ ስላደነቀልኝ በጣም ደስ አለኝ:: ቀጥሎም ወደእነ በዓሉ ግርማ ...

***ያኔ በአካባቢህ የስነጽሑፍ ክበብ ነበር?***

እኔ ተወልጄ ያደግኩት ወልቂጤ ነው:: እና ያኔ እንኳን ላይብረሪ ይቅርና መጽሐፍ መሸጫ መደብሮች አልነበሩም:: በየስንት ወሩ አንዴ ብቅ የሚል እየዞረ የሚሸጥ አንድ ሰው ነበር:: እና ከሱ ነበር መጽሐፍ የምንገዛው:: ታዲያ ሰው ቤት ስሄድ የመጀመሪያ ትኩረቴ መደርደሪያዎችን ማየት ነበር:: ከዛም ካላነበብኳቸው መጽሐፎች አንዱን መርጬ አነብ ነበር:: በማንበብ ረሀብ ውስጥ ስላደግኩ ነው መሰለኝ ፣ ቆይ ሳድግ ትንሽም ቢሆን ቤተ መጻሕፍት

*(ገጽ 5 ይቀጥላል)*

# አዲስ ብዕር




*አርዕስት*
*ከጥቁር ሰማይ ስር*
*ደራሲና አሳታሚ*
*እንዳለጌታ ከበደ*
*የገጽ ብዛት*
*224*
*እትም*
*1996 አዲስ አበባ*
*የጽሑፍ አይነት*
*አጫጭር ልብወለዶች*

ከሀሳቤ ሳይርቅ የኖረ አንድ ፎቶግራፍ አለ፡፡ ወንድ ልጅ ነው፡፡ እድሜው አስር አመት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ራሱን ደፍቶ ፊቱን ሙሉ በሙሉ በልብሱ አንገት ማውጫ ውስጥ ቀብሮታል፡፡ የልብሱን ቀለም መገመት ያዳግታል፡፡ ክብ ሆኖ ከሚታየው ፀጉሩና ጫፉ ብቅ ካለው ቀኝ ጆሮው በስተቀር የልጁ ሰውነት ተሸፍኗል፡፡ እጆቹና እግሮቹ ሳይቀሩ፡፡ ከግራ እግሩ አጠገብ አንድ ደማቅ ቀይ የፕላስቲክ ፈሳሽ መያዣ ይታያል፡፡ ባዶ ነው፡፡ የተደገፈው ግርግዳ እንደ ነገሩ ቀይና አረንጓዴ ተቀብቷል፡፡ ፊት ለፊቱ ያለው ሲሚንቶ በጣም ቆሻሻ ነው፡፡ የለበሰውን ነገር ቀርበው ሲያዩት ዘርዘር ብለው የተቀመጡ ስድስት ጥቁር ክዋክብት ይታያሉ፡፡ መሀል ለመሀል ደግሞ በደበዘዘ ሰማያዊ በትልቁ *አሜሪካ* ተብሎ በእንግሊዝኛ ተጽፎበታል፡፡ በፎቶግራፉ ታች ወገን በእርሳስ *ኢትዮጵያ* ይላል፡፡ ፎቶግራፉ የተነሳው በሙያተኛው ፎቶ አንሺ በሚስተር ጂም ስፔሌን ነው፡፡ አሜሪካዊ ናቸው፡፡

አብዛኛዎቹ ዘመናዊ የአማርኛ መጻሕፍት (በጣም የተዋጣላቸውን ጨምሮ) የተራውን ሰው ሕይወት በሚዳስሱበት ጊዜ እግረ መንገዳቸውን ወይም ሩቅ ሆነው በሚያጎላ መነጽር በመጠቀም አይነት ነው፡፡ ስለዚህም ጎስቋላ ገጸባህሪያት ቅርብ ሆነው አይታዩም፡፡ የሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ድንግዝግዝ ያለ ነው፡፡ የሚያስቡትን አያካፍሉም፡፡ የሚናገሩት አይሰማም፡፡ የሚወሳው ችግር ኑሮው ሻል ባለው፣ በተማረውና በገለልተኛው ግንዛቤ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ለሚያጋጥማቸው የሕይወት እክሎች መፍትሄ ተብለው የሚሰጡት ከኑሮአቸው የሚመነጩ ሳይሆን ከሩቅ የሚወረወሩባቸው ናቸው፡፡ አብዛኛው የተጎሳቆለ ኑሮ ውስጥ በሚዳክርበት አካባቢ የኪነጥበብ ስራዎች ባብዛኛው ሲዳስሱ የኖሩት የጥቂቱን ሻል ያለ ኑሮ ነው፡፡ በቅርቡ ግን አንጋፋና ወጣት ደራሲዎች የተራውን ሰው ሕይወት የጋረደውን የጭጋግ መጋረጃ እየቀዳደዱ የቅርብ እይታዎችን ይጋበዙናል ፡፡ ከአንጋፋዎቹ የፈቃደ አዘዘ <u>ሰሚ ያጡ ድምጾች</u> ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ በ1977 አካባቢ ስለነበረው ረሀብ የገበሬውን ግጥሞች አቅርቧል፡፡

በቅርቡ ደግሞ ቀልቤን የሰረቀው አንድ ስዕል ሲሆን ለኔ የታየኝ እንዲህ ነው፡፡ ጎርፍ ወደ ሞት የሚወስደው ሰው አንድ እጅ አለ፡፡ እጁ የሚወርደውን ዝናም ለመጠለል ዣንጥላውን ወደ ሰማይ ደግኗል፡፡ የስዕሉ ርዕስ አልተጠቀሰም፡፡ ሕይወታችንን በደንብ የታዘበ መሰለኝ፡፡ ወደ ጥፋትና መከራ የሚነዳንን ዋና ዋና ጉዳይ ቸል እያልን ትኩረታችን ሌላ ሌላ ነገር ላይ እንመነዝረዋለን፡፡ ስዕሉን ያገኘሁት <u>ከጥቁር ሰማይ ስር</u> ከተሰኘው የእንዳለጌታ ከበደ መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡ የተሳለው በደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም ነው፡፡ መጽሐፉ እንደ ጉልት እንጀራ ትንሽዬ ነው - አባባሉን ከጸሐፊው ልበደርና፡፡ ቢሆንም የአዲስ አበባ ክረምት ዝናም ዓይነት አንድ ርዕስ ላይ እኝኝ የሚል ሳይሆን ብዙ የተለያዩ የሕይወት ዘርፎችን ይነካካል፡፡ የማረኩኝ ዋና ዋና ገጸባህርያት ሁልጊዜ የምናያቸው ግን የማናስባቸው ናቸው፡፡ የወደቁ የተናቁ ሰዎች ያናግሩናል፡፡ ጓዳቸውን ያስጎበኙናል፤ ገመናቸውን ይገልጡልናል፡፡

> «አረቄ የያዘው ጠርሙስ በመለኪያዎች ተከቦ በትንሽዬ ጠረጴዛ ተጭኖ ጥጉን ይዟል፡፡ ረዘም ያለ ቡራቡሬ አንሶላ አልጋውን ጋርዶታል፡፡ ከጎን በኩልም ግርግዳ ላይ የተሰካውን ምስማር የነከሰ ፎጣ ተንጠልጥሏል፡፡ የፎጣው ጫፍ ቆሽሿል፡፡ እጅ የሚበዛበት ስፍራ፡፡ .... እሷም እንደዚህ ናት፡፡»
>
> <u>ምጣዱ</u> - ገጽ 12

<u>ሲጨልም</u> የተጻፈው ሶስት ገጽ ከግማሽ በማይሞሉ ቃላት ቢሆንም ቁም ነገሩ ሰፊና ረጅም ነው፡፡ ድርብርብ የሕይወት ችግርን «ወደ ሰባዎቹ የሚጠጉ የሚመስሉ አረጋዊ» ባጋጠማቸው ሁኔታ ሰርስሯል፡፡

<u>በሰንበት የተጸነሰው</u> በስድስት አመቱ አቦቸርና በእናቱ መሀል የሚደረጉት የቃላት ምልልሶች አሳዛኝም አስቂኝ ናቸው፡፡የአቦቸርን ቀልዶች ሰው በተሰበሰበበት አካባቢ ማንበብን አልመክርም፡፡ ጮክ ብለው ሲስቁ ጤንነትን የሚያጠራጥር ሁኔታ ውስጥ ይጨምራልና፡፡ የደራሲው ብዕር ሲሻው በተስፋ መቁረጥ የታጠነውን ምድር ትቶ በምሽት ሲኮበልል <u>የሁልጊዜ ፍቅረኞችን</u> ይጋብዘናል፡፡ ተፈጥሮን በሌላ መልክ እንደገና በፈጠረ ልዩ አለም ውስጥ ሲያዝናናን፡፡ ፍርሀትን በቁና ማስታቀፍ ሲያምረው የተጻፈ የሚመስለው ታሪክ <u>ማን ይገደል?</u> ነው፡፡ በህልምና በእውን ያለው መስመር ደብዝዞ ሊጠፋ ምንም ያህል አይቀረውም፡፡ ህልም የሚደምቅበት ሌላው ታሪክ <u>ማስረሻ</u> ነው - እየመረረ በሚጣፍጥ ፍቅር፡፡

<u>ሳምራዊት</u> ሚዛን ስለ ጎደለው አለማችን ስዕል ነው፡፡ በተለይ የአፍሪካ ፎቶግራፍ፡፡ ሁኔታውን በምንረዳበት ጥልቀትና በግል ምላሻችን መለያየት የሚፈጠረውን ግጭት ያሳያል፡፡ ደራሲው የጓደኝነትንና የመተሳሰብን ልዩ ጣዕም ባላሰብነውና ባልጠበቅንበት ቦታ እያጎናጸፈ ልባችንን ያጸዳዋል ፤ መንፈሳችንን ያበራዋል፡፡ በስም የለሿ የ<u>ምጣዱ</u> ሴተኛ አዳሪና የአስተማሪው፣ የ<u>ክፍተት</u> እመጫትና የቤት ሰራተኛዋ፣ በ<u>እንዳልሆነ ሲሆን</u> ውስጥ የሚሆነው የምንተስኖትና (ጓደኞቹ ጭምር) የምሕረት፡፡ ባጠቃላይ ብዙ ቁም ነገሮቹ የአስራ ዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን የሩስያ ጸሐፊዎች ስራዎችን እንድናስብ ይገፋፉናል፡፡

የአቶ እንዳለጌታ ቃላትና አጫጭር አረፍተ ነገሮችን ማንበብ የወይን ዘለላን እንደ ማጣጣም ማለት ነው፡፡ እንደው ጥፍጥ፣ አልጠገብ የሚል ነገር፡፡ በጉልቤ ያልተገደደ በመሆኑ ያረካል፡፡ እንደ ልብ የሚፈልቅ የምንጭ ውሀ ነው፡፡ ታሪኮቹ ትኩረትን የሚማርኩት መጀመሪያው መስመሮቻቸው ላይ ነው፡፡ መልክና ቅርጽ ገለጻ ላይ ወረቀቱንና ቀለሙን አያለፋትም፡፡ አቤት ማልፋት የሚለውን ቃል ጸሐፊው ሲወደው! የአባባሉ ቀለም እስኪለቅ ድረስ፡፡ አባባል ቀለም አለው እንዴ? ባይኖረውም፡፡

(ገጽ 6 ይቀጥላል)

# የሴት ገጣሚያን በአንድነት




አርዕስት
እኛ 170 ግጥሞች
ደራስያን
አረጋሽ ሰይፉ፣ ፈርማዬ አለሙ፣ መቅደስ ጀምበሩ፣ መርከብ ጸጋዬ፣ ሰናይት አበራ፣ ስመኝ ግዛው፣ ዓለምፀሀይ ወዳጆ፣ ከበደች ተ/አብ፣ ጥሩነሽ ይመር፣ ፅጌ አዳፍሬ፣ ሸዋንግዢው በላይነህና ስንዱ ገብሩ
አሳታሚ
ደራስያኑ
የገጽ ብዛት
274
እትም
ጥር 1990 ዓ.ም. አዲስ አበባ
የጽሑፍ አይነት
የግጥም መድበል

ይህ መጽሐፍ ለኅትመት ከመብቃቱ በፊት የሴት ገጣሚያን እየተሰባሰቡ ስራዎቻቸውን በተለያዩ ስፍራዎች ለሕዝብ ማቅረብ ጀምረው ተወዳጅነትን አትርፈው ነበር:: ታዲያ ከየአካባቢያቸው የሚነሳው ጥያቄ በህብረት አብረው መጽሐፍ እንዲያሳትሙ የሚገፋፋቸው ሆነ:: የማሳተም ውሳኔ ላይ እንደደረሱም በደብዳቤና በስልክ እኔም አብሬያቸው እንድሳተፍ ጋበዙኝ፤ ደስታዬን ገልጬ ከማዕዱ ተቋደስኩ:: <u>የኢትዮጵያ የሴት ደራሲያን ማኅበር</u> በሚል ጥላ በማሰባሰብና በማጠናከር ግንባር ቀደሙን ሚና ትጫወት የነበረችው አረጋሽ ሰይፉ ጥረቷ ተሳክቶ መጽሐፉ ለአንባብያን ቀረበ::

በኢትዮጵያ ህብረተሰብ በደቦ እርሻ ማረስ፣ በጋራ ተሰባስቦ መፍተል፣ በህብረት ችሎት መሰየም በአንድነት መመገብ ያለና ተወዳጅ ባህል ነው:: በስነጽሑፍ ረገድም ይህ በኢትዮጵያ ሶስተኛው የግጥም መድበል ሲሆን ከዚያም በፊት በሰላሳ አምስት ወጣቶች የተጻፈው ከ1928 ዓ.ም. ጀምሮ የነበሩትን ግጥሞች ያሰባሰበው መድበል ዓይነት የደራሲያንን ስብስብ ስራ ማሳተም በሌላው አለም የተለመደና የተወደደ ተግባር ነው:: ሌላው ቀደም ብሎ በህብረት ከታተሙ የደራስያን ስራ ውጤቶች አንዱ <u>ፅጌረዳ ብዕር</u> የሚለው ነው::

<u>እኛ 170</u> የሚለው የግጥም ስብስብ ስራ ግን በቋንቋው ጥራትና መጣፈጥ በሀሳቡ ብስለትና አቀራረብ ከፍተኛ ግምት ሊሰጠው ይገባል ባይ ነኝ:: በመጽሐፉ ሽፋን ጀርባ ላይ የሰፈረውን ቀንጭቤ ልጥቀስ «... ፍቅርን፣ ተስፋን፣ ችግርን፣ ደስታን፣ ሀዘንን፣ እምነትንና ሌላውንም የህይወት መልክ በኪናዊ ለዛ አሳይተዋል» ይላል የሙሉመቤት ዘነበ እውነት የተሞላ አስተያየት:: በመጽሐፉ ውስጥ የሰፈሩት ሀሳቦች ከግል ፍቅርና ክህደት፣ ከተራ ወሬና ወረት፣ ስለወገንና ሀገር ጭምር ያላካተቱት ርዕስ የለም:: የሰርካለም ተፈሪ የሽፋኑ ስዕል መስህብ አለው:: ጮራ የፈነጠቀባት እንስት ኢትዮጵያዊት ባህሏን ተላብሳ በእንዝርቷ እየጻፈች የምታገኘውን ብርሀን መልሳ ስትረጭ የሚያሳይ ትርጉም ስዕል ነው:: በሁሉም የሙያ ዘርፍ ኢትዮጵያዊ ሴቶች መኖራቸውን ለማመልከት ይመስላል ስራው ሁሉ በእንስት ጾታዎች የተጠቃለለ ነው::

ከሀገሬ ከወጣሁ በኋላ የፈሩትን ድንቅዬ ወጣት ብዕረኞች ከመጠቃቀሴ በፊት መጽሐፉ ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ከነበሩት ከነወይዘሮ ሸዋንግዢው በላይነህና ከታዋቂዋ አርበኛና ብዕረኛ ከ ወ/ሮ ስንዱ ገብሩ ጨምሮ ለትውልድ መተላለፍ የሚገባውን የብዕር ውጤት ሁሉ አካቷል::

«ፈጣሪህን አስብ ልብህን አትዝጋ
በጊዜህ ሥራበት እንድታገኝ ዋጋ::»
ጥሩነሽ ይመር (ገጽ 235)

ይህ የወል ግጥም በሚባል የሚታወቀው የግጥም አይነት ነው:: የመጽሐፉ ስብስብ ስራ ማር ማር የሚልና የሚጥም በመሆኑ አንዱን አውስተው አንዱን ለመተው ቢያስቸግርም ጥቂቶቹን ላነሳሳ::

አረጋሽ ከግል የውበት ግምገማዋ ስታካፍለን <u>አንዳንዴ</u> በሚለው ግጥም ውስጥ

«ዓይንን ተከዋክብት፣ ያስተካክልና፣
ጥርስን ተከናፍር፣ ያሸሞነሙንና፣
የሚቀዳ ላህይ፣ የሚጨለፍ ፀዳል፣ ያኅናጽፍና፣
ከራስ እስከ ጥፍር፣ ውበት ይቀባና፣
ያን ተክለ ሰውነት፣ ያንን ውብ ቁመና፣
አድርጎት ይቀራል ....
የማስተዋል ምስኪን፣ የመገንዘብ ወና:: »
(ገጽ 32)

እያለች ትደረድረዋች:: በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን የእኔነት መጥፎ በሽታ በምሬት ጠቋቁማለች:: ቁጣዋን ለመረዳት ብዙ አይፈጅም:: <u>የደራ ገበያ</u> ትለውና

«... ቅዠቱ አይጣል እንጂ የፍጻሜው ነገር፣
ባቋራጭ ያከብራል ............
ሕሊናን መቸብቸብ... ሕሊናን መቸርቸር::»
(ገጽ 25)

ብላ በብዕሯ ትጋረፋለች::

ጽሑፍን በቀልድ አሽሞንሙኖ ህብረተሰብን ማስተማር የተካነችው ፈርማዬ አለሙ የምትታወቀው ፈገግታን በማጫር ነበር:: ፈርማዬ በድንገተኛ በሽታ ሕይወቷ እስካለፈ ጊዜ ድረስ በየመድረኩ ተጋብዛ የዝግጅት ድምቀት ሰጪ ፋና ነበረች:: በዚህ መድበል ውስጥ <u>ቆሞ መቅረት</u> በሚል ርዕስ

«... ምናል ቆሞ መቅረት--ከሥፍራው መገኘት
ግጥምጥም እንዲሉ በተፈለጉ ለት::»
(ገጽ 76)

እያለች በባህላችን አስነዋሪ የሚባለውን ጉዳይ በቀልድ ከሽና ሙግቷን አደባባይ አቅርባዋለች:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዕረኞቻችን ላይ የሚታይ መከፋት መቆጨት መመረር በእነዚህም ብዕረኞች ጉልህ ሆኖ ይታያል::

<u>ይሞታል</u> በሚል ርዕስ ሰናይት አበራ ከቋጠረችው ጥቂቱን ልደርድር::

«... ቆስቋሹም ከረሳው--እሳቱን አዳፍኖ
አስታማሚ ሲያጣ--ለማገገም ድኖ
እሱም እንደወተተ--ፍልት ግንፍል ብሎ
ስሜትም ይሞታል! --በስሜት ተገድሎ::»
(ገጽ 158)

ብላ ታዘንበዋለች::

በዚህ መጽሐፍ ሌላዋ የማደንቃት ከበደች ተክለአብ ትገኝበታለች:: በተደጋጋሚ ስራዋ በመደነቅ ስለተገመገመ የዕድሉን ቅድሚያ ለሌሎች ለመስጠት ብዬ አላነሳሁትም:: የጊዜን ፍሬያማነትም ሆነ ብኩንነት

(ገጽ 6 ይቀጥላል)

# ግራጫ ቃጭሎች

<u>ግራጫ ቃጭሎች</u>ን በምን መልክ እንደምናቀርብላችሁ ጨንቆን ነበር፡፡ የድርሰቱ ታላቅነት ተሰምቶን የሚገባውን ሂስ በሙያተኛ ለማጻፍ ሞክረን ነበር፡፡ ቢሆንም እንደኛው በመጠኑ ዳስሶ መተዉ ከብዷቸው ቀረ፡፡

አዳም ረታ ይህ ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍ የመጀመሪያ ስራው አይደለም፡፡ ከዚህ ቀደም በ1970ዎቹ ከሌሎች ደራስያን ጋር በታተመው <u>አባ ደፋር</u> በተሰኘው የአጫጭር ታሪኮች መድበል፣ በ1981 ዓ.ም. ደግሞ <u>ማህሌት</u> ብሎ የሰየመውን የአጭር ታሪክ ስብስብ አቅርቧል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪም በተለያየ መጽሔቶችና ጋዜጦች ካቀረባቸው ሥራዎቹ ውስጥ በ1982 በብሌን (የኢትዮጵያ ደራስያን ማህበር ልሳን) መጽሔት ያቀረበው <u>ጫጉላ - ወደፊት - ወደኋላ</u> የሚጠቀስ ነው፡፡ <u>ግራጫ ቃጭሎች</u> በደራሲው ከተጻፈ 15 ዓመታት ቢያልፈውም ለኅትመት ሊበቃ የቻለው ገና ባሳለፍነው አመት ነበር፡፡

መጽሐፉ በሌሎች ልብወለድ ስራዎች የተለመደውን በትልም ላይ የተመሠረተ ትረካ አይከተለም፡፡ ይበልጥኑ የሚያተኩረው አካባቢውንና ገጸባህሪያቱን እንደ ሰዓሊ ወይ ፎቶ አንሺ በመቅረጽ ላይ ነው፡፡ አንዳንድ ተደራሲያን ይህ የአጻጻፍ ዘይቤ የታሪኩን ግስጋሴ ሊገታ ይችላል ቢሉም ደራሲው ይህን በመከተል ውስብስብ የሆነ ሥዕላዊ ገለጻ ለመሳል ያመቸዋል፡፡ በዚህም ዘይቤ የተካነ ደራሲ የአንደኛ መደብ ትረካን (በገጸባህሪው አንደበት) ሲጠቀም ዋናውን ገጸባህሪ የማይረሳ ባለታሪክ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ፋና ወጊ ድርሰት ዙሪያ ሰፊ ውይይት ለሚመጣው እትማችን እያቆየን ለአሁኑ በሚከተሉት ስዕላዊ ገለጻዎች እንለያይ፡፡

«ልብ ወለድ የቀለጠ ፋንታሲም ቢሆን ማሕበራዊ መነሾ አለው፡፡ ... እዚህ ፈጠራ ውስጥ የተፃፈው ታሪክ በሙሉ ከላይ እስከ ታች <u>መዝገቡ ዱባለ</u> ይመስገንና ቅጥፈት ነው፡፡ በተአማኒ ቅጥፈት ውስጥ እውነትን ለመንገር፡፡»

መግቢያ

### ቅርጽ

«የዚህን መፅሐፍ የአፃፃፍ ቅርፁን የተዋስኩት ከእንጀራ ቅርጽ ነው፡፡ በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ያሉት ምዕራፎች ከእንጀሪው ጠቃጠቆ/ንዑስ ፍሬዎች ጋር ወይም ከእንጀራው ዓይኖች ጋር እንዲማሰሉ ሆኖ ነው የቀረበው (አንድ ዐይን ወይም ጠቃጠቆ እንደ አንድ ምዕራፍ)፡፡»

መግቢያ

### ዋናው ገጸባህሪ ስለራሱ

« «ሲወለድ የተረገመ ነው» ሲሉኝ እሰማ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ጊዜ ጭር ያለ ሜዳ ላይ የራሴን ስም ከፍ አድርጌ ጠራሁ፡፡ «መዝገቡ!! መዝገቡ!» (እንጀራ እናቴ) ስሜን ሁልጊዜ ስትጠራው ተነጫንጫ ነበር፡፡ እግዜር ግን ስሜን ሲጠራው ቀስ ብሎ ነው፡፡ መ ፡፡ ዝ ፡፡ ገ ፡፡ ቡ፡፡ ብሎ ነው መ - መይሳው ማለት ይሆናል፡፡ መ - መከረኛው ሊሆን ይችላል፡፡ ዝ - ዝምተኛው፡፡ ገ - ገላጩ፡፡ ቡ - ቡቃያው፡፡»

ገጽ 9

### ነፋስ መውጫ

«ረባም አልረባም በዚህም በዚያም ብሎ ታዲያ ከተማዋ መስቀለኛ መንገድ ይበዛታል፡፡ ከተማዋ ውስጥ በጠቅላላ ሁለት የመኪና ባለቤቶች ስድስት የብስክሌት ባለቤቶች አሉ፡፡ ጌኛ (ከብት) መዓት ነበር፡፡ አደጋም ይበዛል፡፡ ታዲያ




አርዕስት
ግራጫ ቃጭሎች
ደራሲ
አዳም ረታ
አሳታሚ
ሻማ ቡክስ
የገጽ ብዛት
462
እትም
፲፱፻፺፯ አዲስ አበባ
የጽሑፍ አይነት
ረጅም ልብወለድ

ዋናው የትራፊክ አደጋችን በአህያ የሚመጣ ነበር፡፡ ስንጎዳም በደወል የሚፈውስ እንደ ሐኪም ቤት የሚያገለግል ቤተክርስቲያን ነበረን፡፡ በጎዳና ላይ መወዝወዝ ስለማበዛ በአህያ ተረግጬ መታመሜ አይቀርም ብዬ በመፍራት በዚያ ቤተክርስቲያን አጠገብ ካለፍኩ ደወሉን ልጎበኝ ጎራ እል ነበር፡፡»

ገጽ 199

### ስለ ፈረንጆች አገር

«አንድ እዚያ ንፋስ መውጫ ዘመዶቹን ሊጠይቅ ከዩኒቨርስቲ የመጣ ሰው ሲያወራ ነበር አሉ፡፡ አባቴ ጋ ፀጉሩን ሊስተካከል ሄዶ «ፈረንጆች አገር የብዙ ቤቶች እርዝመት ከዚያ ይበልጣል» ብሎ ወደ ጎለልታ የተራራ ጉብታ እየጠቆመ አሳይቶአቸው በከተማው ሲያስወሩለት ነበር፡፡ አባቴ ኮስተር ብሎ ታዲያ፡ «እንዲህ እንዲህ ከጎለልታ የረዘመ ቤት ከበዛማ የፈረንጅ ቆለኛ የለውም ማለት ነው» አለው አሉ፡፡»

ገጽ 202

### የማንበብ አባዜ

«የብርሀኑ ዘሪሁንን መጽሐፍ (ጨረቃ ስትወጣ) ሶስተኛ ጊዜ አነበብኩት፡፡ ፈጣን አንባቢ ሆኛለሁ፡፡ ይህ ብርሀኑ የሚባለው ሰውዬ በጣም አስማተኛ ነው፤ በጣም የሚጣፍጥ ታሪክ ይጽፋል .. ማታ ጨረቃ ስትወጣ ለማየት ስጠብቅ አመሸሁ .. እኔ ብቻዬን ጨረቃ ስትወጣ ዛፍ ስር ተቀምጬ አስባለሁ፡፡ ተሰምቶኝ የማያውቅ ነገር አደረብኝ .. ሴት ጓደኛ ያስፈልገኛል፡፡

ብሬ አስማተኛ ናት፡፡ «ጽጌሬዳ በሌላ ስምም ቢሆን መዓዛውንና ውበቱን አይለውጥም» ትላለች ብርሀኑ፡፡ መዝገቡ መዝገቡ ነው እንደ ማለት ነበር፡፡»

ገጽ 163-6

# ቆይታ ከእንዳለጌታ ...

(ከገጽ 1 የቀጠለ ...)

እከፍታለው የሚል ስሜት ነበረኝ:: አስራ ሁለተኛ ክፍል ስጨርስም ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የሚያስገባ ነጥብ አልነበረኝም:: እና ያኔ ትንሽዬ ክፍል ውስጥ መጽሐፎቼን አሰባስቤ ማከራየት ጀመርኩ - ለ 24 ሰአት 25 ሳንቲም:: እዛም ብዙ ሰዎች - ተማሪዎች መምህራን - ይመጣሉ፤ መወያየት ጀመርን:: ከዛም ተስፋ ቡክ ክለብን ከፈትን፤ የስነጽሑፍ ሰዎችን የሚያበረታታ እንዲሁም የቀለም ተማሪዎችን የሚያግዝ አንዳንድ ስራዎችን መስራት ላይ አተኩረን ነበር::

***ወደ አዲስ አበባ እንዴት መጣህ?***
መጽሐፍ በማከራየት የሰበሰብኩትን ገንዘብ ይጌፍ ዕቁብ በመግባት አንድ ሶስት ሺ. ብር ሲሞላ ወደ አዲስ አበባ ተጓዝኩ:: ፍላጎቴ ስነጽሑፍ መማር ቢሆንም ይህን ዘርፍ የሚያስተምር የግል ተቋም ስላልነበረ ዩኒቲ ኮሌጅ በመግባት ጆርናሊዝም እና ኮምዩኒኬሽን ተማርኩ::

***የመጀመሪያ መጽሐፍህስ?***
መጀመሪያ ገንዘብ ስሰበስብ መማር ላይ አተኮርኩ:: ቀጥሎ ደግሞ ወልቂጤ የነበረውን ስራ ወንድሞቼ ያግዙኝ ነበረ እና ገንዘቡ ሲጠራቀም የኔን ስም የያዘ መጽሐፍ ለማሳተም የነበረኝን ፍላጎት እውን ለማድረግ አሰብኩ:: አንዳንድ አጫጭር ልብወለዶቼ ከዚህ በፊት አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ወጥተው ነበር፤ ጓደኞቼ እንዲሁም የማከብራቸው ሰዎች ጥሩ አስተያየት ሰጥተውኝ ነበር:: ነገር ግን እነዚህ አጫጭር ልብወለዶች ተሰባስበው አንድ የራሴ የሆነ ቀለም ማሳየት እፈልግ ነበር፤ እንዴት እንደማስብ ማሳየት እፈልግ ነበር:: መጀመሪያ ግጥም ለማሳተም አሰብኩ:: ያኔ ግን ብዙ ገጣሚዎች ስራዎቻቸውን ለንባብ ያበቁበት ጊዜ ነበረና አይ አጫጭር ልብወለድ ቢታተም በአመት አንዴ ነውና ለምን የኔዎቹን ሰብስቤ አላሳትማቸውም ብዬ አሰብኩ:: ከዚህ በፊት ለንባብ ከበቁትና ከአዳዲሶቹም ጨምሬ አሥራ ስድስቱን አብሬ አሳተምኩ:: ከጥቁር ሰማይ ሥርንም ለማሳተም የፈጀብኝ 12 ሺ. ብር ነው - ግማሹን ከኔ ግማሹን ተበድሬ::

***ምን ያህል ኮፒ አሳተምክ?***
ሶስት ሺ:: ሰዎች፣እኔም ጭምር፣ አይሸጥም ብለን ፈርተን ነበር:: መጀመሪያ የተበደርኩትን ገንዘብ ካስመለስኩ ጥሩ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፤ ከዛም ካልከሰርኩ ጥሩ ነው አልኩ:: ቀስ በቀስ ጋዜጦች ስለመድበሉ መጻፍ ሲጀምሩ እንዲሁም ሰው ሲነጋገርበት ስመለከት አይ ትንሽ እንኳን ማትረፍ ብችል ማለት ጀመርኩ:: አሁን መጽሐፉ ከወጣ ሁለት ዓመት አልፎታል እና ገበያ ላይ አለ ማለት ያስቸግራል:: ባለፈው አንድ ሱቅ ውስጥ ሁለት ሶስት አይቼ እራሴ ገዟኋቸው:: እና አሁን አብዛኛው ጸሐፊ አንድ ወይም ሁለት ሺ. በሚያሳትምበት ጊዜ ሶስት ሺ. ማሳተሜ ብዙ ቢመስልም ከሰባ ሚልዮን ህዝብ በላይ ባለበት ሀገር እንዲህ መሆኑ ንባብ በጣም ማሽቆልቆሉን ያሳያል::

***ከጥቁር ሰማይ ሥር ዋጋው አስር ብር ነው:: ለመሆኑ የአከፋፋዮቹ ድርሻ እንዴት ነው?***
አከፋፋዮቹ 30 ከመቶ ያገኛሉ:: የሽፋን ስዕሉንና layout ለማሰራት፣ ታይፕ ለማስደረግ፣ እንዲሁም ለማሳተም ለእያንዳንዱ መጽሐፍ 4 ብር ወጥቷል:: አከፋፋዮቹ ደግሞ 3 ብር ያገኛሉ:: እኔ ደግሞ ለሰዎች በነፃ የሰጠሁትን እንዲሁም የተበላሹትን ኮፒዎች አስበህ ከያንዳንዱ መጽሐፍ 2.80 አገኛለሁ::

***በአንድ ጋዜጣ ላይ ምኞትህ አንድ አገራዊ ድርሰት በሚልዮን ኮፒ እንዲታተም መሆኑን ገልጸህ ነበር:: እዛ ለመድረስ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?***
ምን መሰለህ! ብዙ ሰዎች መጽሐፍ የሚያነቡት በሌላው ጎትጓችነት ነው:: በአሁኑ ሰዓት መጽሐፎች ውድ ናቸውና «ሳንቲሜን አውጥቼ ከገዛሁ በኋላ የፈለኩትን ያህል ደስታ ባላገኝበትስ? ዝም ብሎ እንቶ ፈንቶ ቢሆንስ?» የሚል አስተያየት አለ:: አንዳንዶች «ለመሆኑ በአሁኑ ዘመን ጥሩ ደራሲ አለ ወይ?» ይላሉ:: እናም በዚህ ጥርጣሬ አይገዛም ማለት ነው:: የሰዉን ስሜት ስመለከት መምህሩ አንብቡ ያላቸውን መጽሐፍ ውለው ሳያድሩ ያነባሉ:: ምክንያቱም ካላነበቡ የሚጎድልባቸው እንዳለ ስለሚያውቁ ነው::

ሁለተኛ ደግሞ ያሉን የቤተመጻሕፍት ቁጥር ብዛታቸው ስንት ነው ብንል መልሱ ያሳዝነናል:: መጽሐፍ ሻጮችንም የሚያበረታታ አካል የለንም:: ከሚልዮን በላይ ኮፒ ቢታተም ደስ ይለኛል ያልኩት ከምን አንጻር ነው ቢባል? እንግዲህ የህዝቡን ብዛት አስብ! በየጊዜው ደግሞ የመኃይማኑ ቁጥር ቀንሷል ነው የሚባለው:: ይህን ህልም እውን ለማድረግ የንባብንና የውይይት ክበቦችን ማብዛት የራሱ አስተዋጽዖ ይኖረዋል:: ምክንያቱም ብዙ ዎቹ ያነቡና የሚያዋራቸው ሰው የለም፤ የሚያወያያቸው ሰውም የለም:: በአሁኑ ሰዓት የአንባቢው ቁጥር አንሷል ማለት አስቸጋሪ ነው:: ሰዉ ወደ ጋዜጣና መጽሔት፣ የዕለት ተዕለት ወደሆነ ኑሮ የሚያተኩሩ ዜናዎችን ለማንበብ ነው የሚረባረበው:: መንግሥት በየቀበሌው ካሉት የመዝናኛ ማዕከሎች መሐል የተወሰኑትን ለንባብ አገልግሎት እንዲውሉ ቢያደርግ የአንባብያን ቁጥር ማብዛት ይቻላል:: ምክንያቱም ወመዘክር ወይም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብትሄድ ሰልፉ ሌላ ነው:: እንኳንስ ቁጭ ብለህ ልታነብባቸው ይቅርና ሰው በዝቶባቸው የማይመቹ ቦታዎች ሆነዋል::

ከደራሲው ብዙ የሚጠበቅ አይመስለኝም - ማለት እንዲነበብለት:: የውይይትና የንባብ ክበባት ይህንን ነገር ማጉላትና ማራመድ ይችላሉ:: በመገናኛ ብዙኃን የጥበባት ፕሮግራምም አዳዲስ መጻሕፍት ሲወጡ በማስተዋወቅ የአንባብያን ቁጥር እንዲበዛ ማድረግ ይቻላል:: የቴሌቪዥን ሚድያ ስናይ የስዕል ኤግዚቢሽን ሲከፈት ሮጠው ያቀርባሉ፤ ጥሩ ነው ደስ ይላል:: ደራስያን መጽሐፍ በሚያስመርቁበት ሰዓት ግን ብዙ አይመጡም:: አንባቢንና ድርሰትን ለማገናኘት የሚያደርጉት ጥረት የደከመ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ:: እነዚህ ሁሉ ድክመቶች መቀረፍ ቢችሉ በተወሰነ መንገድ የአንባብያንን ቁጥር ማብዛት እንደሚቻል አስባለሁ::




በ1998 ዓ.ም. የታተመው የእንዳለጌታ ከበደ አዲሱ ረጅም ልብወለድ::

(ገጽ 7 ይቀጥላል)

# አዲስ ብዕር..

(ከገጽ 2 የቀጠለ ...)

ደራሲው ልብ ሰቀላ፣ ግጭት ፈጠራንና ያልተጠበቀ መደምደምያን ተክኖበታል። ገጸባህርያቱ፣ በዝርዝር የተሳሉት አከባቢያቸውና ቃል ምልልሶቻቸው ከስነልቦናዊ ገጽታቸው ጋር የቀረቡት ከፍ ባለ ውበትና ጥራት በመሆኑ ወጣቱ ጸሐፊ ይህን ሁሉ ብቃት «ከወዴት ዘረፈው?» የሚያሰኝ ነው።

በቅርቡ ሽጋ ሽጋ የአማርኛ ስራዎች ለኅትመት መብቃታቸው የአጋጣሚ ነገር ወይም ሊታወቁ የሚችሉ ምክንያቶች ውጤት ይሆን? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሌሎችስ ጥሩ ጥሩ ስራዎች መታተም ሲችሉ በተለያዩ እንቅፋቶች ተዳፍነው ቆይተዋል ወይ? በከፍተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ያለው አስተዋፅኦ ምንድነው? የመጻሕፍት ክበባት ብቅ ብቅ ማለት የመልካም ጸሐፊዎች መፈጠር ምክንያት ናቸው ወይስ ውጤት ሊሆን ይችላሉ? ወይስ ሁለቱን? በፍጥነት የሚቀያየረውና የሚዘበራረቀው ማህበራዊ አከባቢያችን ምን አይነት አስተዋፅኦ አለው? እነኚህና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ለስነጽሁፍ ተመራማሪዎች መተው ይበጃል።

(ከአሸናፊ ዋቅቶላ)

# የሴት ገጣሚያን..

(ከገጽ 3 የቀጠለ ...)

የዘመንን ውጤታማነትና ምንነት የትውልድን ስኬታማነት ገላጩ ብዕር ነው። ታዲያ ብዕርም እንደ አንድ ፍጡር በብዕረኛ ዐይን ሲገመገም የጊዜን መራራነት ለችሎት የሚያቀርብበት ሁኔታ አለ። እንዴት? ቢሉ የመቅደስ ጀምበሩን «እሱም አለቀሰ» ያነቧል...

«... ያሳሰበው ሲጻፍ...
ያሰበው ተውጦ
እውነት ሲጨነግፍ...
እብለት ሲታይ በልጦ
...
እቁር ቀለም ሳይሆን...
ደም እያፈሰሰ...
ብዕር አለቀሰ።»
(ገጽ 108)

እንግዲህ በዚህና በመሰል ግሩም ስነግጥሞች መዋልም ማምሸትም መክረምም መኖርም ይቻላል። እኔ ከረሀብ ሁሉ የምፈራውና የምጠላው የመንፈስን ረሀብ ስለሆነ ነው መሰል ይህን ዓይነት መጽሐፍ አጠገቤ ካለ በተራብኩ ቁጥር አነሳዋለው። ያላነበበው እንዲያነበው እየጋበዝኩ ወደ መደምደሚያዬ ላምራ። ያለ እንጂ፣ የሞላ እንጂ፣ የከበረ እንጂ፣ የደረጀ እንጂ የሌለ መቼስ መቼስ ቢሆን ምኑ ይሰረቃል? ለዚህ አይደል ስመኝ ግዛው «ምን ልጠብቅ?» ያለችው።

«...ዱካህን ተከተልኩና ቀዬህንም ቃኘሁት
አይኔን በሩቅ ወርውሬ ቀልቤን ከደጅህ አዋልኩት
...
የት አለህና ተዘርፈሃል
ሰርቀው አሚጠውሃል
የለህምና እንግዴህ ዘብ መቆሜ ለምኑ ነው
አናህ አይጠበቅ?
ውልቅህ አይነካ?
ባዶህ አይሰረቅ?»
(ገጽ 184)

ቸር ይግጠመን።

(ከዓለምፀሀይ ወዳጆ)

# "የት ይሆን ያነበብኩት?"

(ይህ አምድ ብርቅዬ የሆኑ የስነጽሑፍ ስራዎችን የምንዘክርበት ነው።)

ባለፈው እትማችን ላወጣነው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አልደረሰንም። ታዲያ እንዲያ ተሽሞንሙና የቀረበችው ገጸባህሪ የአማርኛ መጀመሪያ ልብወለድ ላይ የተሳለችው *ጦቢያ* ናት። ደራሲውም አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ነበሩ። መጽሐፉም በሮማ በ1900 ዓ.ም. በድሬዳዋም በ1919 ዓ.ም. የታተመው <u>ልብ-ወለድ ታሪክ</u> የተባለው ድርሰታቸው ነው። አብዛኞቻችን ግን የምናውቀው በድጋሚ እትሞቹ ላይ በወጣው <u>ጦቢያ</u> በሚለው ርዕስ ነው።






ቀዳሚ ሀያሲ ፕሮፌሰር ታምራት አማኑኤል በ1936 ባዘጋጁት <u>ስለኢትዮጵያ ደራስያን</u> በሚለው ጽሑፋቸው ስለ አፈወርቅ ገብረኢየሱስና መጽሐፋቸው እንዲህ ብለዋል -

«<u>ልብወለድ ታሪክ</u> ለኢትዮጵያ የሮማን (ልብወለድ) መጀመሪያ መጽሐፍዋ ነው። ከዚህ በፊት እንዳመለከትሁት፤ ያገራችን ደራሲ አሳቡን በጽሕፈት ለመግለጥ ባሰበበት ጊዜ ባሳቡ የሚፈጥራቸው ሰዎች የግብራቸውን ስም፤ የተጸውዖ ስም አድርጎ «አቶ መልካም ሰው፣ አቶ ክፉ ሰው» የሚሉትን አካሄድ ብቻ ይከታተል ነበር። (ያሁኑ ጸሐፊ ግን) የፕሮፌሰር አፈወርቅንና የኤውሮፓን መጻሕፍት በማንበቡ ልብ ወለድ ታሪክ ለመጻፍ ይጣጣራልና በር ከፋቹ ፕሮፌሰር አፈወርቅ በመሆናቸው ምስጋና ይገባቸዋል።

ፕሮፌሰር አፈወርቅ ... አንባቢው ሳይሰለች አሳባቸውን እንዲያስተውል አድርገዋል። ሙሉ ንግግራቸው ያማርኛን ባሕርይ እየተከተለ በረዘመበት ጊዜም ቢሆን፣ ግልጥና የጣፈበት ነው። አንዳንድ ጊዜ ብቻ ቅጽል ሲያበዙ ነገሩ ጉት ይሆንባቸዋል። ፕሮፌሰር አፈወርቅ በደራሲነታቸው ሙቀት ያለበት ንግግር ማምጣት ዋና ባሕርያቸው ነው። ሙቀቱም የሚገባ ወይም ተሽጋጋሪ በመሆኑ፣ አንባቢው አሳባቸውንም በማይቀበልበት ጊዜ መሞቁ አይቀርም። በጽሑፍ ሥራቸው የሚያነሱት ሰው ወይም እንስሳ፣ ጫካ ወይም በረኻ ሁሉም ሕይወት ያለበት ሁኖ ይታያል።»

## አዲሱ ጥያቄ

በዚሁ እትማችን የምናቀርበው ጥያቄ ከስነግጥም ጋር የተገናኘ ነው። ምንም እንኳን ግጥም በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ረዘም ያለ የእድገት ታሪክ ቢኖረውም እስከዛሬ ድረስ በጣት የሚቆጠሩ ደራሲያን ናቸው ስራዎቻቸውን በመጽሐፍ መልክ ደጋግመው ያቀረቡልን።

ከሁለት በላይ የግጥም መድበሎችን ካወጡ የአገራችን ደራሲያን መሀል የሶስቱን ስምና የመጽሐፎች አርዕስት ዝርዝር ለላኩልን ሁለት አባላት የዮሐንስ አድማሱን <u>እስኪ ተጠየቁን</u> እንሸልማለን።

*መልሶቻችሁን ከልሳናችን ጀርባ በሚገኘው አድራሻ ይላኩልን።*

# ስለ ድርሰት ምን ተብሏል?

(ይህ አምድ ሀያስያን ስለ ስነጽሑፍ የጻፉትን የምንጠቅስበት ነው።)

በዛሬ አምዳችን ሁለት ቀደምት ምሁራን ከ60 እና 35 አመታት በፊት የጻፉትን ሒስ እናቀርባለን። ሁለቱም በሕይወት ባይገኙም ያኔ ያሰፈሩት አስተያየት በሚገርም መልክ ዛሬም ያስተጋባል።

ፕሮፌሰር ታምራት አማኑኤል በ1936 ዓ.ም. ባዘጋጁት ስለኢትዮጵያ ደራስያን ከሚለው ጽሑፋቸው የሚከተለውን ቀንጭበናል።

> «የአማርኛ ቋንቋ ከብዙው ሕገጋቱ አንዱ፣ ማሰርያ አንቀጽን ከንግግር መጨረሻ ማግባት ነው። ከጽሕፈት ላይ ባንድ ማሰርያ አንቀጽ ውስጥ ባሉት ቃላት ማኽል ጣልቃ እያገባ ልዩ ልዩ አሳብና ንግግር በሚጨመርበት ጊዜ ዋናውንና ጣልቃ የገባውን ከውኖ ለማስተዋል እንዲመች ሊያደርጉ የቻሉ ስጦታ ያላቸው ደራስያን ብቻ ናቸው። ደራሲው ሙሉውን ንግግር ባማርኛ ባህርይ በሚያስኬድበት ጊዜ ደግሞ ሰነፍ አንባቢ እንዳይታክተው ለማድረግ ያሰበበት እንደሆን ፣ ንግግሩን ባጭር ባጭሩ በማሰሩ ላንባቢ መመቸቱ እርግጥ ነው።
>
> ቢሆንም ደራሲ በፊተኛው (በረጅሙ) አካሔድ ሲጽፍ፣ አንባቢው በውጥን ጭርስ አካሔድ አስሮ ለንግግሩ ደራሲው ያላሰበውን አሳብ ከመስጠት የሚደርስበት ጊዜ አለ።ደራሲው በሁለተኛው አካሔድ (ባጭሩ) ሲጽፍ፣ አንባቢው አሁን ካመለከትነው ስሕተት አይደርስም፤ ግን ንግግሩ በአንድ ማሰሪያ አንቀጽ ሊጠቀለል ሲቻል፣ ደራሲው እያቋረጠ በመናገር አንደበቱን ያልረታ ሕፃን ሊመስል ነው። ንግግሩም በመጠኑ ካማርኛ ባሕርይ የራቀ ሊያደርገው ነው። ዋና ደራሲ የምንለው፣ በረጅሙም ሆነ በአጭሩ አካሄድ ጽፎ፣ ንግግሩ ግልጽና ጣዕም ያለው ሲሆን ነው።»

ዮሐንስ አድማሱም እስከ 1961 ዓ.ም. የወጡትን ስራዎችና የአገራችንን የሒስ ባህል ሲተች -

> «በባህላችን የሒስ ጥበብ አልነበረም፣ የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። ከዚህም የተነሳ ደራስያኑ መጻሕፍታቸው በጋዜጣም ሆነ በመጽሔት ሲተቹ/በቀጥተኛ ሒስ/ አንዳንዶቹ ያኮርፋሉ አንዳንዶቹ ይዝታሉ፤ አንዳንዶቹ በጋዜጣም ሆነ በመጽሔት ይሳደባሉ። ይኸ መንፈስ ከየት እንደመጣ አላውቅም። ጉዳዩ ጥልቅ ምርመራና ጥናት የሚያስፈልገው ነው። ይሁን እንጂ አንድ የማውቀው ነገር አለ። ሒስ በቅኔ ቤት የተለመደ ነው። የቅኔው ተማሪ ከቅኔው ትምህርት ሌላ በጥበቡ የሚኅለምሰው የኪነት ተውህቦውን የሚያተባው የሚያራቅቀውና የሚያደራጀው በሒስ ጥበብ ነው። የተማሪውን ቅኔ የቀለም ጓደኞቹና መምህሩ ይተቻሉ። እሱም እንደዚሁ ያደርጋል። ተማሪዎቹ የመምህራቸውን ቅኔ ይተቻሉ፤ አንዳንዴም ብትንትኑን ያወጡታል። ኩርፊያና ስድብ ዛቻና ቂያሜ የለም። ይህ መልካም ጥበብ እያለ ደራሲያናችን ለምን በሒስ ይቆጣሉ?
>
> የቅኔ ቴክኒክ አለ። ይኽንንም ቴክኒክ ማወቅ የማንኛውም ደራሲ በተለይም የገጣሚ ተግባርና ግዴታ ነው። ሌሎችም ብዙ የጽሑፍ ቴክኒክ ከሀገራችን በብዛት ይገኛሉ። የተረት፣የሙሾ፣ የእንቆቅልሽ፣ የእንካሰላንቲያ፣ የቀረርቶ... ወዘተ። እነዚህን ሁሉ አንቱ የሚባል ወይንም ለመባል የሚሻ ደራሲ አጠናቆ ማወቅ ግዴታው ነው።
>
> ሒስ ለስነጽሑፍ ሕይወት መጠበቂያ አይነተኛ ፍቱን መድሃኒት ነው። ሒስ ጉድለትንም ጥራትንም መግለጫ ጥበብ ነው። ማስተማሪያም ነው። እንደ ስድብ እንደ ነውር መቆጠር የለበትም። በሒስ መስታወትነት ስጋውን የማይከላ ስነጽሑፍም ሆነ ደራሲ ከበድን አንድ ነው፤ ተገቢ ቦታውም ቤተ መዘክር ነው።»

# ቆይታ...

(ከገጽ 5 የቀጠለ ...)

ሣህለሥላሴ ብርሃነማርያም አንድ ዝግጅት ላይ ጥናት አቅርበው በደርግ ዘመን ብዙ አንባቢዎች ነበሩ ብለዋል። ለምሳሌ የሲሳይ ንጉሡ ሰመመን 70-80 ሺ ኮፒ ታትሞ ተሸጧል። አሁን ግን ደራሲዎች የሚያሳትሟቸው መጽሐፎች ከ5ሺ ኮፒ ብዙም ፈገግ አይሉም። ለምንድነው? አስበው እንግዲህ የህዝብ ቁጥር ጨምሯል ነገር ግን የአንባቢያን ቁጥር እየቀነሰ ነው። ያኔ ጎትጓች ነበረው። ያሁኑ ያህል ጋዜጦች አልነበሩም፤ ሚዲያ አልነበሩም፤ ኢንተርኔት ጊዜን አያጣብም ነበር። ሲኒማዎችም አልተበራከቱም። አቶ ሣህለሥላሴ ሲናገሩ ያኔ ጋዜጦች «ወታደሩ ስለማያነብ ንቃተ ህሊናው አልዳበረም» እያሉ ይወርፉ ነበር። ወታደሩም እኛ ነን ወይ የማናነበው፤ እኛ ነን ወይ ንቃተ ህሊናችን ያልዳበረው በማለት መጽሐፍ ይገዛ ነበር፤ ይላክለትም ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ወታደሩ እንዲያነብ ግፊት ስለሌለው የተወሰነ አንባቢዎችን አጥተናል ሲሉ ሰምቻለሁ።

***አንተ፣ በዕውቀቱ ሥዩምና አማኑኤል መሃሪ ስትረዳዱ ይታያል። ከጥቁር ሰማይ ስር ውስጥ ያሉትን ስዕሎች የሳለውም በዕውቀቱ ነው። የደራሲዎች መተባበርና አብሮ መስራትን እንዴት ታየዋለህ?***

አብሮ መስራት ስራውን የተሻለ ለማድረግ ምንም ጥርጥር በሌለው መልክ ያግዛል። ለምሳሌ በዕውቀቱ ኗሪ አልባ ጎጆዎች የሚለውን መጽሐፉን ከማውጣቱ በፊት አንዳንድ ግጥሞቹን እንዲያወጣ መክረነው ሀሳባችንን ተቀብሏል። ይህ ትውልድ ውስጥ መንፈሳዊ የሆነ ስሜት አለ፤ እርስ በእርስ የመተጋገዝ ነገር አለ። ከሶስተኛው መጽሐፌ ቀደም ብሎ በዕውቀቱ መጽሐፍ ቢያወጣ ደስ ይለኛል። ሙሉ ትኩረታችንንም እዛ ላይ አድርገን ብንሰራም በጣም ደስ ይለኛል። ምክንያቱም እሱ የሚጽፋቸውን ነገሮች እወዳቸዋለሁ። የኔ መጽሐፎችንም ሳሳትም በዕውቀቱ የራሱ የሆነ እገዛዎች ነበሩት፤ አብዛኞዎቹን ሀሳቦቹን ተቀብያቸዋልሁ። ስለዚህ የምጽፈው ጽሑፍ ወደ ህዝብ እንዲደርስ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በእኛ መሀከል መተጋገዙ ጥሩ ነገር ለህዝብ ለማቅረብ ከመጓጓት ስሜት ነው። ፍቅርህን የምትገልጸው የምትወደውን ነገር የሚወዱ ሰዎች በማብዛት ነው። እኔና ጓደኞቼ ጥበብን እንወዳለን፤ ኪነትም የተለየ ስሜት ይሰጠናል። በጣም ጥሩ ነገር ስናዘጋጅ እንቀባበላለን፤ ለምን ይሄ ነገር ጋዜጣ ላይ አይወጣም እንላለን። የህብረት መዝሙር ላይ ከሚሳተፉ ሰዎች መሃል እንደ አንዱ ነን፤ እያንዳንዱ ዘማሪ የራሱ የሆነ ድምጽ አለው። በሁሉም ባንመሳሰልም አንድ ላይ ስንደረደር ግን እራሱን የቻለ ጥዑመ ዜማ ሊወጣ እንደሚችል እንገምታለን። መተባበራችን እገዛ እንደሚያደርግ እገምታለሁ፤ ቢያንስ ቅንነትን ለተተኪው ትውልድ ማሳየት ነው።

እናመሰግናለን።

# ዜና አንድምታ

ክበቡ ጉዞ ከጀመረ እነሆ ሶስት ወር በሚሆን ጊዜ ያቀደውን ዓላማዎች ቀስ በቀስ መተግበር ጀምሯል:: በአሁኑ ጊዜ ሃምሳ ስምንት ከፋይና ሁለት የክብር አባላት አሉት:: የስነጽሑፍ ሂስ ያዘሉ ሁለት ልሳን አቅርቧል:: እንዲሁም በSeattle እና Washington D.C. አካባቢ የሚገኙት የክበቡ አባላትና የስነጽሑፍ አፍቃሪያን በተመረጡት መጻሕፍት ዙሪያ ስብሰባ አድርገዋል::

ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ካሉት ባልደረቦቻችን ጋር በመተባበር ክበቡ የመጀመሪያ መጽሐፉን ለማሳተም በቅቷል:: በኩር መጽሐፉም በራሪ ቅጠሎች ሲሆን በወጣቱ ደራሲ በዕውቀቱ ሥዩም ቀደም ብሎ ታትሞ ከስርጭት ጠፍቶ ስለነበረ ክበቡ 2000 ቅጂ ለማሳተም ችሏል::

**ነፃ አባልነት ከፈለጉ!**

ባለፉት ሳምንታት አብዛኞቻችሁ ለሰጣችሁን አስተያየት እያመሰገንን በሚቀጥሉት ወራት ክበቡ የአባላቱን ቁጥር ለመጨመር መዘጋጀቱን ሊነግራችሁ ይወዳል:: አባላትነታችሁን ያለክፍያ ማራዘም/መጀመር እንድትችሉ መንገድ አበጅቷል:: አሰራሩም እንዲህ ነው:: እርስዎ በሚያመጡት እያንዳንዱ አባል ልክ ክፍያዎ $10 እየቀነሰ ይመጣል:: በተጨማሪም የስጦታ አባልነትና የተማሪ ቅናሽ እንደምናቀርብ ልንገልጽ እንወዳለን::

**ሰሜን አሜሪካ በ1998 ዓ.ም. ከቀረቡ መጻሕፍት በከፊሉ**







**The Texture of Dreams**
ከፋሲል ይትባረክ
**(773) 883-9818**
info@nyalapublishing.com

**ክንዕቅቦምን ክንነጽጎምን ዘለና ባህልታት**
(መንከባከብና ማስወገድ ያለብን ባህሎች)
ከገላውዴዎስ አርአያ
**(203) 789-1990**
webmaster@africanidea.org

**ፈተና**
(የግጥም መድበል)
ከቴዎድሮስ አበበ
(703) 973-1896
info@tewodros.com

**ኢትዮጵያ በ1998 ዓ.ም. ከታተሙ መጻሕፍት በከፊሉ**

**ልብወለድ**

- ሙሽት - በጌታቸው ሀይሉ
- ህልመኛው - በሙሉጌታ ጉደታ
- ከሩት በስተጀርባ - በቢንያም የማነ እንቁስላሴ
- ዛጎል - በእንዳለጌታ ከበደ

**ግጥሞች**

- አሻራ - በተስፋዬ ብርሀኑ
- ኤፍራጦስ - በቸርነት ወልደገብርኤል
- የተፈሩ ህልሞች - በአንዷለም ይስሐቅ

**ጥናታዊ ስራዎች**

- የቀኃሥ ፍጻሜና የደርግ አነሳስ - በአሐዱ ሳቡሬ
- የአገው ህዝብና የዛጔ ሥርወ መንግስት ታሪክ - በአያሌው ሲሳይ
- የደረስኩበት (ግለ ታሪክና ትዝታዎች) - በማሞ ውድነህ
- እንጎቻ (ታሪኮችና ቀልዶች) - በአባይነህ አበራ

በየሶስት ወሩ የሚታተም
የኢትዮጵያውያን መጻሕፍት ክበብ
የስነጽሑፍ ልሳን

በመስከረም ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ተመሠረተ

አዘጋጆች

ሚካኤል እንዳለ
ብሩክ አብዱ
ትዕግስት በላቸው
ኅሩይ አብዱ
ኤፍሬም ግርማ

አሳታሚ

የፊደል ሠራዊት ማኅበር
Committee for Ethiopian Literacy

አባልነት

Committee for Ethiopian Literacy
Andemta Club
P.O.Box 391
Boston, MA 02215

info@ethiopianbooks.com

ስልክ፡ (617) 331-7282

ጽሑፍ ለማበርከት ወይንም አባል ለመሆን ከፈለጉ ከላይ ባለው አድራሻ ይጻፉልን::

ስለ የፊደል ሠራዊት ማኅበር

የዛሬ 41 አመት በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ይህን ማኅበር አቋቋሙ:: አላማው በኢትዮጵያ ይካሄድ የነበረውን የብሔራዊ ፊደል ሠራዊት ሥራ በገንዘብና በአቅም ማገዝ ነበር:: በኢትዮጵያ ውስጥም የፊደል ብቻ ሳይሆን የሒሳብና የጤና ትምህርት እንዲስፋፋና ወደ 2 ሚልዮን ሕዝብ አንባቢ እንዲሆን አስተዋጽኦ አደረጉ - ያኔ:: ዛሬ ደግሞ ከሀገር ውጭ ያሉትን ኢትዮጵያውያን ከሀገራቸው ጸሐፊዎች ጋር ለማስተዋወቅና ለማቀራረብ የያኔ አቻዎቻችንን አደራ ተቀበልን::

የደራሲነት መብት ካልተነፈገ እንዲሁም ጽሑፎቹን በሞላ ከተነበቡ ልሳኑን አባዝቶ ለሰው ማደል የአንባቢው መብት ነው::